# HEALTH CARE CONNECT

## የቤተሰብ ሃኪም ወይንም ነርስ ፕራክቲሽነር ለማግኘት እንድትችሉ ለመርዳት

**ontario.ca/healthcareconnect**

*ሄልዝ ኬር ኮኔክት የቤተሰብ ጤና እንክብካቤ አቅራቢ የሌላቸው ሰዎች የጤና ተንከባካቢ እንዲያገኙ ይረዳል።*

### ሄልዝ ኬር ኮኔክት እንዴት ነው የቤተሰብ ጤና እንክብካቤ አቅራቢ እንድታገኙ የሚረዳው?

ሄልዝ ኬር ኮኔክት የቤተሰብ ጤና እንክብካቤ አቅራቢ የሌላቸው ሰዎች በ አካባቢያቸው የሚገኝ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ እንዲያገኙ የሚረዳ ፕሮግራም ነው። ፕሮግራሙ በሽተኞችን የሚቀበሉ ሃኪሞችን እና ነርሶች ፕራክቲሽነሮችን ካገኘ በኋላ የቤተሰብ ጤና እንክብካቤ አቅራቢ ከሚያስፈልጋቸው ሰዎች ጋር ያገናኛል።

### በፕሮግራሙ መሳተፍ እንዴት ይቻላል

ለሄልዝ ኬር ኮኔክት መመዝገብ ቀላል ነው።
በ1-800-445-1822 ስትደውሉ የምታገኙት ሰው የተወሰኑ ጥያቄዎችን ይጠይቃችሁ እና ለፕሮግራሙ ይመዘግባችኋል። በኢንተርኔትም በመጠቀም የሚከተለውን ድረገጽ በመጠቀም መመዝገብ ትችላላችሁ፡
**ontario.ca/healthcareconnect**

### ሄልዝኬር ኮኔክት የቤተሰብ ጤና እንክብካቤ በፍጥነት ለሚያፈጋቸው ሰዎች ቅድሚያን ይሰጣል።

ቅድሚያ የሚሰጠው በጣም ከፍተኛ የሆነ የጤና እንክብካቤ በፍጥነት ለሚያፈልጋቸው ነው።

በአካባቢያችሁየቤተሰብ ሃኪም ወይንም ነርስ ፕራክቲሽነር እንደተገኘ ወዲያውኑ ይነገራችኋል።

*ሄልዝኬር ኮኔክት እናንተን ለመርዳት ዝግጁ ነው።.*
*ነገር ግን እናንተም በበኩላችሁ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ መፈለግ አለባችሁ።*

### ስለ ሄልዝኬር ኮኔክት ምን ማወቅ አለባችሁ

- ሄልዝኬር ኬር ኮኔክት የቤተሰብ ሃኪም ወይንም ነርስ ፕራክቲሽነር በምትፈልጉበት ጊዜ በፍለጋ ይረዳችኋል።
- መገኘት መቻሉን ግን ዋስትና መስጠት አይችልም። ስለዚህ እናንተም በበኩላችሁ ፍለጋውን መቀጠል አለባችሁ።
- የኦሂፕ ቁጥር ያስፈጋችኋል።

### ኬር ኮኔክተር የቤተሰብ ጤና እንክብካቢ አቅራቢ በምትፈለጉበት ጊዜ ይረዳችኋል።

ሄልዝኬር ኮኔክት ከተመዘገባችሁ በኋላ በአካባቢያችሁ የሚገኝ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ለማግኘት የሚረዳ ነርስ (ኬር ኮኔተር በመባል የሚጠራ/የምትጠራ)ይመደብላችኋል።

| ሄልዝኬር ኮኔክተር እና እናንተ<br>የምትገኙበት መንገድ (አድራሻችሁ፣ ስልካችሁ..) ወይንም<br>የጤናችሁ ሁኔታ ከተቀየረ ለሄልዝኬር ኮኔክተራችሁ አስታውቁ። |
|---|

**ሃኪም ወይንም ነርስ ፕራክቲሽነር ያስፈልጋችኋልን?**
**በ 1-800-445-1822 ይደውሉ ወይንም የሚከተለውን ድረገጽ ይጎብኙ ontario.ca/healthcareconnect**

Amharic – Health Care Connect Cat# 012544 Revised December 2010 © Queen's Printer for Ontario

Ontario